የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

## OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

ስድስተኛ አመት ቁጥር ፶፱
አዲስ አበባ ሚያዝያ ፪ ቀን ፪ሺ፮

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Sixth Year No. 59
ADDIS ABABA April 11, 2014

**ማውጫ**

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአስፈጻሚ አካላት አደረጃጀትና መዋቅር ጥናት ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት ደንብ.................ገጽ ፯፻፳፯**

**CONTENT**

**The Executive Organs Structural Study Project Office of Addis Ababa City Government Regulation.............................page 727**

## ደንብ ቁጥር ፶፱/፪ሺ፮
## የአስፈጻሚ አካላት አደረጃጀትና መዋቅር ጥናት ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት ለማቋቋምና አሰራሩን ለመወሰን የወጣ ደንብ

የአዲስ አበባ ከተማ ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታዋ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ በመምጣቱ፣ የነዋሪዎቿ የአገልግሎት ፍላጎት በአይነትና በብዛት እየጨመረ በመሄዱና እንዲሁም የአገልግሎት ማግኛ መንገዱም በዚያው መጠን ዘመናዊ፣ ቀልጠፋና በቀላሉ ተደራሽ ማድረግ በማስፈለጉ፤

በነዋሪው የዕድገት ፍላጎት መሰረት የከተማዋን አስተማማኝ የመፈፀም እና የማስፈፀም አቅም ለማሳደግና ተቋማዊ ለውጥን ለማረጋገጥ የአደረጃጀት መዋቅርን መከለስ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

እንዲሁም ከተማዋ እየተጓዘችበት ላለው የልማት ጎዳና ሊመጥን የሚችል የአደረጃጀትና መዋቅር ጥናት በማጥናትና ተግባራዊነቱን በማረጋገጥ የዜጎችን ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት ማጎልበት በማስፈለጉ፤

## Regulation No. 59/2014
## A Regulation to Provide for the Establishment and to Determine the Working Procedures of the Addis Ababa City Government Executive Organs Structural Study Project Office

**WHEREAS**, the strategic importance of Addis Ababa City has been growing steadily, the residents' need for services has been increasing both in variety and quantity and the method of getting service accordingly needs to be modern, fast and easily accessible;

**WHEREAS**, to develop reliable execution and implementation capacity and realize institutional change it is found necessary to revise the organizational structure of the City to fit to the development demand of the residents;

**WHEREAS**, it is found necessary to strengthen the citizen being overall beneficiary by conducting organizational and structural study that is compatible to the development truck in which the City is and assuring its implementation;

ያንዱ ዋጋ
Unit price

አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፳፬፵፭
Addis Negari Gazeta P.O.Box 2445

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚና ማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፴፭/፪ሺ፬ አንቀጽ ፷፬ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአስፈጻሚ አካላት አደረጃጀትና የመዋቅር ጥናት ፕሮጀክት ጽህፈት ቤትን ለማቋቋምና አሰራሩን ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር ፶፱/፪ሺ፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ትርጓሜ

በዚህ ደንብ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጓሜ የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡-

፩. **"ከተማ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤

፪. **"አስተዳደር"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

፫. **"ከንቲባ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ነው፤

፬. **"ቢሮ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአቅም ግንባታ ቢሮ ነው፤

፭. **"አደረጃጀት"** ማለት አንድ የመንግስት ተቋም የተቋቋመለትን ዓላማ በአግባቡ ለማከናወን የሚያስችለው መዋቅር፣ የሚያከናውናቸውን ተግባራት፣ ተጠያቂነታቸውን፣ የሰው ኃይላቸውን፣ የእርስ በእርስ ግንኙነታቸውን አስፈላጊነት እንዲሁም የውስጥና የውጭ ግንኙነት የሚያመላክትና አንድ መስሪያ ቤት ሊከተለው የሚገባውን አቅጣጫ በግልጽ የሚያስቀምጥ አወቃቀር ነው፤

፮. **"ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት"** ማለት በዚህ ደንብ አንቀፅ ፫ የተቋቋመው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአስፈጻሚ አካላት አደረጃጀትና የመዋቅር ጥናት ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት ነው፡፡

**NOW, THREFORE,** in accordance with Article 64 of the Addis Ababa City Government Executive and Municipality Service Organs Re-establishment Proclamation No. 35/2012 the Cabinet hereby issued this Regulation as follows.

## PART ONE
## GENERAL PROVISIONS

### 1. Short Title

This regulation may be cited as "The Addis Ababa City Government Executive Organs Structural Study Project Office Establishment and Working Procedure Regulation No. 59/2014"

### 2. Definitions

In this Regulation unless the context requires otherwise:

1. **"City"** means Addis Ababa City;
2. **"Government"** means the Addis Ababa City Government;
3. **"Mayor"** means Mayor of Addis Ababa City;
4. **"Bureau"** means Capacity Building Bureau of the Addis Ababa City Government;
5. **"Structure"** means a structure that a certain government institution has to follow in order to carry out the ideals of its foundation, activities it undertakes, its accountability, importance, human resources, interaction, internal and external interaction and a structure that sets the path for a certain government institution which it needs to follow;
6. **"Project office"** means the Addis Ababa City Government Executive organs Organizational and Structure Study Project Office established in accordance with Article 3 of this Regulation.

**፫. ስለ መቋቋም**

፩. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአስፈጻሚ አካላት አደረጃጀትና የመዋቅር ጥናት ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት (ከዚህ በኋላ ‹‹ጽህፈት ቤት›› እየተባለ የሚጠራ) ህጋዊ ሰውነት ያለው የአስተዳደሩ መስሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፤

፪. የጽህፈት ቤቱ ተጠሪነት ለቢሮው ይሆናል፤ ሆኖም ቢሮው በውክልና ጽህፈት ቤቱ አግባብነት ላለው አካል ተጠሪ እንዲሆን ሊያደርግ ይችላል፤

፫. የጽህፈት ቤቱ አድራሻ በከተማዉ ውስጥ ይሆናል፡፡

**፬. የተፈፃሚነት ወሠን**

ይህ ደንብ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር በሚገኙ የመንግስት አስፈጻሚ ተቋማት እና የከተማው አስተዳደር የልማት ድርጅቶች ላይ ብቻ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የጽህፈት ቤቱ ዓላማ፣ አደረጃጀት፣ ስልጣንና ተግባር

**፭.ዓላማ**

ጽህፈት ቤቱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

፩. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውጤታማና ቀልጣፋ አገልግሎት ለነዋሪዎች መስጠት እንዲችል ነባሩን አደረጃጀት በመፈተሽ የተሻለ እና ብቃት ያለው አደረጃጀት መፍጠር፤

፪. የከተማ አስተዳደሩን ልዩ ልዩ አካላት ተጠሪነትና ሚና በጥናት አስደግፎ መለየት፤

፫. ለእያንዳንዱ የአስተዳደሩ አካል ዓላማውን መፈፀም የሚያስችል ብቃት ያለው የሰው ሃይል መለየት እና ተገቢውን የአሠራር ሥርዓት መጠቆም፤

**3. Establishment**

1. The Addis Ababa City Government executive organs structure study project office, hereafter called “office”, is hereby established as an institution of the City Government having its own legal personality;
2. The office shall be accountable to the Bureau; however, the Bureau may delegate to an appropriate organ;
3. Address of the office shall be within the City.

**4. Scope of Application**

This Regulation shall be applicable only to the executive institutions and enterprises of the Addis Ababa City Government.

## PART TWO

## OBJECTIVE, STRUCTURE, POWER AND FUNCTION OF THE OFFICE

**5. Objective**

The office shall have the following objectives:

1. Creating better and efficient structure by examining the existing one with the view of enabling the Addis Ababa City Government render efficient and fast service to the residents;
2. Identifying accountability and role of the different organs of the City Government based on research;
3. Identifying capable human resource and pinpointing the appropriate working procedure to each organ of the Government to enable it accomplish its objective;

፬. የከተማው አስተዳደር የጀመራቸውን የልማት፣ የመልካም አስተዳደር እና የለውጥ ስራዎችን ወደ ላቀ ደረጃ ማሸጋገርና ቀጣይነቱን ማረጋገጥ ናቸው፡፡

፮. **<u>አደረጃጀት</u>**

ጽህፈት ቤቱ ተጠሪነቱ ለቢሮው ሆኖ የሚከተለዉ አደረጃጀት ይኖረዋል፡-

፩. ስትሪንግ ኮሚቴ፣

፪. ስራ አስኪያጅ፣

፫. እንዲሁም ሌሎች ለጽህፈት ቤቱ የሚያስፈልጉ ሃላፊዎችና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

፯. **<u>የስትሪንግ ኮሚቴ አባላት</u>**

ስትሪንግ ኮሚቴው የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

፩. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ… ሰብሳቢ

፪. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ጽህፈት ቤት ኃላፊ…………….. ምክትል ሰብሳቢ

፫. የአዲስ አበባ ከተማ አቅም ግንባታ ቢሮ ኃላፊ …ጸሃፊ

፬. የአዲስ አበባ ከተማ ፍትህ ቢሮ ኃላፊ …………አባል

፭. የአዲስ አበባ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ኃላፊ……………………………………….. አባል

፮. የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ከተማ ልማት፣ ኮንስትራክሽንና ቤቶች ልማት ሚኒስቴር ተወካይ………… አባል

፯. የጠቅላይ ሚኒስቴር ጽህፈት ቤት ተወካይ…አባል

፰. **<u>የስትሪንግ ኮሜቴ ተግባርና ኃላፊነት</u>**

፩. በከተማዋ የሚጠናውን አደረጃጀትና መዋቅር በበላይነት ይመራል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣

፪. በከተማ ደረጃ የሚጠናው መዋቅር ልማታዊና ዲሞክራሲያዊ መሆኑን ያረጋግጣል፣ ይደግፋል፣

4. Promoting and ensuring sustainability of the development, good governance, change activities that the City Government has commenced.

6. **<u>Structure</u>**

The office, being accountable to the Bureau, shall have the following structure:

1. Steering Committee,
2. Manager, and
3. The necessary officials and supporting staff.

7. **<u>Steering Committee Members</u>**

The steering committee shall have the following members:

1. Mayor of Addis Ababa City…….Chair person;
2. Head of Addis Ababa City Mayor Office ……………………………….....deputy chairperson
3. Head of the Addis Ababa City Capacity Building Bureau …………….…………………...secretary
4. Head of the Addis Ababa City Justice Bureau ……………………………………..…..member
5. Head of the Addis Ababa City Finance and Economic Development Bureau………member
6. A representative of the FDRE Ministry of Urban Development, Construction and Housing Development ………….…………………..member
7. A representative of Office of the Prime Minister ……………………………...member.

8. **<u>Function and Responsibility of the Steering Committee</u>**

1. Superiorly control, follow up and lead the structural study of the City;
2. Ensure and support that the structural study being carried out at city level is developmental and democratic;

፫. በፌደራል ደረጃ የወጡ ፖሊሲዎችን የሚያስፈጽም መዋቅር መሆኑን ያረጋግጣል፤

፬. በፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ ስራ አስኪያጅ የሚቀርብለትን ወቅታዊ ሪፖርት ያዳምጣል፣ ግብረ መልስ ይሰጣል፤

፭. የመዋቅሩን የጥናት ውጤት ከልማትና ፖሊሲዎቻችን ጋር ተቀናጅቶና ተሳስሮ የሚተገበርበትን አቅጣጫ ያስቀምጣል፣ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፣ ድጋፍ ያደረጋል፤

፮. የመዋቅር ጥናቱ በፌደራልም ሆነ በከተማ ደረጃ ከወጡ ህጎች ጋር የማይቃረን መሆኑን ያረጋግጣል::

## ፱. የአቅም ግንባታ ቢሮ ተግባርና ኃላፊነት

፩. የከተማው አስፈጻሚ አካላት መዋቅር ጥናት በተቀናጀ መልኩ እንዲፈጸም ሙያዊ ምክርና ዕገዛ ያደርጋል፤

፪. በጥናቱ ሂደት በቴክኒካል ጉዳዮች ላይ ያጋጠሙ ችግሮችና ጉድለቶች ላይ የመፍትሄ ሃሳብ ያቀርባል፤

፫. በሚመለከተው አካል ፀድቆ የቀረበውን መዋቅር በተቀናጀ ሁኔታ ተግባራዊ ያደርጋል አፈፃፀሙንም ይከታተላል፡፡

## ፲. የጽህፈት ቤቱ ተግባርና ሀላፊነት

፩. በከተማ አስተዳደሩ አጠቃላይ ዓላማና ተግባራት ላይ በመመሰረት አደረጃጀቱን መፈተሸ፣ የተቀናጀ ስልጣንና ኃላፊነትን በግልፅ ሊያሣይ የሚችል ድርጅታዊ መዋቅር ተጠንቶ በስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣ አገልግሎት መስጠትን እስከ ማስጀመር ያለውን ሂደት ይከታተላል፤

፪. የተዘጋጀውን አደረጃጀት ውጤታማነትን የሚያረጋግጡ ዑደቶቹን ለማስቀጠል የሚያስፈልጉ መነሻ የፖሊሲ የህግና የስታንዳርድ ማዕቀፎችን እንደ የአግባቡ ይቀርጻል፤

3. Ensure that the structure enables execution of policies issued at federal level;

4. Hear the timely reports presented by the Manager of the project office and gives feedback thereof;

5. Puts direction towards the integrated and coordinated implementation of the study result with the development and policies; follow up the implementation thereof and support same;

6. Ensure that the structural study does not contradict to the laws enacted at federal as well as city level.

## 9. Function and Responsibility of Bureau of Capacity Building

1. Give professional advice and support towards integrated execution of the structural study of the executive organs of the City;
2. Submit solution for technical problems and failures encountered in the course of the structural study;
3. Implement the structure, approved by the concerned body, in an integrated manner and follow up its application.

## 10. Function and Responsibility of the Office

1. Revise the structure of the City Government based on the overall objective and function; cause an organizational structure, that can display integrated power and responsibility, is studied and implemented; follow up the process until commencement of service;
2. Design, as may be proper, initial policy, legal and standard frameworks that are necessary in order to ensure the effectiveness of the prepared structure;

፫. ፕሮጀክቱ ለሚጠናቀቅበት ጊዜ አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት በማድረግ ለሚረከበው የአስተዳደሩ አካል ዝርዝርና ግልጽ የሆነ የተሟላ የርክክብ ሰነድ በማዘጋጀት በይፋ የፕሮጀክቱን የስራ ሂደት ማጠናቀቅ፣

፬. የፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱን አፈፃፀም አስመልክቶ ወቅታዊ ሪፖርት ለቢሮው እና ለሚመለከተው አካል ማቅረብ፣

፭. ዓላማውን ለማስፈፀም የሚረዱት ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

**፲፩. <u>የስራ አስኪያጁ ሥልጣንና ተግባር</u>**

፩. የጽህፈት ቤቱን ስራ በበላይነት ይመራል ያደራጃል፣ ያስተዳድራል፣ ይቆጣጠራል፣

፪. ለአደረጃጀቱና ለመዋቅሩ የሚያማክሩ አማካሪዎችን ይመድባል፣ ይሾማል፣ ያሰናብታል፣

፫. የአደረጃጀት ስራው በታቀደለት ጊዜ እንዲጠናቀቅ የቅርብ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፣

፬. የጽህፈት ቤቱን የአደረጃጀት መዋቅርና የሰው ሀይል ፍላጎት፣ ኃላፊነትና ድርሻ፣ ደመወዝና አበል በማጥናት ያዘጋጃል፣ በቢሮዉ አማካይነት ለከንቲባዉ በማቅረብ ያስፀድቃል፣ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፣

፭. የጽህፈት ቤቱን የአጭርና የመካከለኛ ጊዜ ዕቅድና በጀት እንዲሁም የስራ መርሃ ግብር አዘጋጅቶ ለቢሮው ያቀርባል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፣

፮. የጽህፈት ቤቱን በጀት፣ የሰው ሃይል እና ግብዐት ያስተዳድራል፣ ይቆጣጠራል፣

፯. በስትሪንግ ኮሚቴ የሚተላለፉ ውሳኔዎችን ይፈጽማል፣ ያስፈጽማል፣

፰. ሌሎች በቢሮው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፡፡

3. Make necessary preparation to the completion of the project and prepare detailed, clear and full-fledged handover document to the organ of the City Government that takes over; and finalize the process of the project officially;
4. Submit timely report to the Bureau and the concerned body about performance of the project office;
5. Carryout such other activities that help achieve its objective.

**11. <u>Power and Function of the Manager</u>**

1. Superiorly lead, organize, administer, and control activities of the project office;
2. Deploy, appoint or remove councilors to the structural study;
3. Make close follow up and support towards the timely accomplishment of the structural study;
4. Prepare, based on study, the organizational structure, human resource demand, job description, salary and per-diem of the Office and submit to the Mayor, through the Bureau, for approval; implement same upon approval;
5. Prepare and submit to the Bureau the short and medium term activity plan and budget as well as work schedule; implement same upon approval;
6. Administer and control the budget, human resource and material resources of the Office;
7. Execute and cause the execution of decisions made by steering committee;
8. Perform such other activities designated by the Bureau.

## ክፍል ሶስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፲፪. የገንዘብ ምንጭ**

የጽህፈት ቤቱ የገንዘብ ምንጭ በከተማዉ አስተዳደር ከሚመደብ በጀት ይሆናል፡፡

**፲፫. መመሪያ የማውጣት ስልጣን**

የከተማው አስተዳደር አቅም ግንባታ ቢሮ ይህንን ደንብ ለማስፈጸም የሚረዳ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፲፬. የሂሳብ መዛግብት አያያዝ**

፩. ጽህፈት ቤቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብትን ይይዛል፤

፪. የጽህፈት ቤቱ የሂሳብ መዛግብት፣ ገንዘብ እና ንብረት ነክ ሰነዶች አያያዝና አጠባበቅ የከተማውን አስተዳደር ህግ የተከተለ ይሆናል፤

፫. የጽህፈት ቤቱ የሂሳብ መዛግብት፣ ገንዘብ እና ንብረት ነክ ሰነዶች ቢሮው ወይም የከተማው አስተዳደር በሚሰይማቸው ኦዲተሮች ይመረመራል፡፡

**፲፭. የጽህፈት ቤቱ ተግባር የሚቋረጥባቸው ምክንያቶች**

የጽህፈት ቤቱ ተግባር ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ሊቋረጥ ይችላል፡-

፩. ጽህፈት ቤቱ የተቋቋመበት ዓላማ ሲሳካ፣

፪. የተቋቋመበት ዓላማ የማይሳካ ወይም ሊፈፀም የማይችል ሲሆን፡፡

**፲፮. የመተባበር ግዴታ**

ጽህፈት ቤቱ ለዚህ ደንብ አፈጻጸም በሚያደርገው እንቅስቃሴ ሁሉ የከተማው አስተዳደር የመንግስት ተቋማትና የልማት ድርጅቶች ተገቢውን ትብብር የማድረግ ግዴታና ሃላፊነት አለባቸው፡፡

## PART THREE

## MISCELLANEOUS PROVISIONS

**12. Financial Source**

The financial source of the office shall be from budget allocated by the City Government.

**13. Power to Issue Directive**

The Capacity Building Bureau of the City Government may issue a directive that helps implement this Regulation.

**14. Keeping Books of Account**

1. The office shall keep full-fledged and eligible books of account;
2. The keeping of books of account, financial and property related documents shall be in accordance with the laws of the City Government;
3. The books of account, financial and property related documents of the Office shall be audited by auditors nominated by the Bureau or the City Government.

**15. Reasons for Termination of Function of the Office**

Function of the office may terminate due to one of the following reasons:

1. Where the objective for which office is established is accomplished;
2. Where the objective for which it is established becomes impossible.

**16. Duty to Cooperate**

The government institutions and enterprises of the City Government are duty bound to cooperate with the Office in its effort towards implementation of this Regulation.

**፲፯. <u>የፕሮጀክ ጽህፈት ቤት የቆይታ ጊዜ</u>**

የፕሮጀክቱ የቆይታ ጊዜ ደንቡ በአዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለተከታታይ ስድስት ወራት ሲሆን እንደአስፈላጊነቱ የከተማው አስተዳደር ሲወስን ለተወሰነ ጊዜ ሊራዘም ይችላል፡፡

**፲፰. <u>ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች</u>**

ይህንን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራር በዚህ ደንብ የተደነገጉትን ጉዳዮች በተመለከተ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

**፲፱. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ በአዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

**አዲስ አበባ**
**ሚያዝያ ፬ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም**

**ድሪባ ኩማ**
**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**

**17. <u>Duration of the Project Office</u>**

Duration of the project shall be six months from the date of publication of this Regulation in the Addis Negari Gazette; however it may be extended further based on decision of the City Government.

**18. <u>Inapplicable Laws</u>**

Any regulation, directive or traditional practice contrary to this Regulation shall not be effective regarding matters provided by this Regulation.

**19. <u>Effective Date</u>**

This Regulation shall enter into force as of the date of publication in the Addis Negari Gazette.

**Done at Addis Ababa**
**On this 11th day of April, 2014**

**Diriba Kuma**
**Mayor of Addis Ababa City**